# የቅድመ ግብር ክፍያ ስርዓት አፈጻፀም ዙሪያ

## ለግብር ከፋዮች የቀረበ የግንዛቤ ማስጨበጫ

መ.መ.ቁ 2/2011

መግቢያ

- ተቀንሶ የሚያዝ ታክስ (Withholding Tax) ማለት በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ክፍል አስር መሰረት "ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ ተቀንሶ መያዝ ያለበት ታክስ ነው"

1. በኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ ግዥ ወይም በአንድ የእቃ አቅርቦት ውል ከ10 ሺ ብር በላይ ለሆነ ክፍያ ወይም በአንድ የአገልግሎት ውል ከ3,000 ብር በላይ ለሚፈፀም ክፍያ ለሻጩ/አቅራቢው ከሚከፈለው ክፍያ ላይ 2% ቀንሰው በመያዝ ለባለስልጣኑ ግብር የመክፈል ግደታ አለበት።
2. ማንኛውም ግብር ቀንሶ የማስቀረት ኃላፊነት የተጣለበት ሰው ከ 10,000.00 ብር በላይ የዕቃ ግዥ እንዲሁም ከ3000 ብር በላይ አገልግሎት ግዥ የፈፀመ እንደሆነ በፈፀመው ግዥ መጠን ቅድመ ታክስ ግብር በመቀነስ ማሳወቅ የሚጠበቅበት መሆኑን እየገለጽን ንግድ ፍቃድ እና ቲን ሰርተፍኬት ካላቸው ሰዎች የተገዛ ግዥ ከሆነ 2% ካልሆነ 30% በመቀነስ ግዥው ከተፈፀመበት ቀጥሎ ባለው ወር ገቢውን ማሳወቅ የሚጠበቅበትመሆኑን እየገለጽን

- የቤት ኪራይ አገልግሎት እና ባለስልጣኑ ባወጣው የታክስ ደረሰኝ አስተዳደር መመሪያ መሰረት የግዥ ማረጋገጫ ደረሰኝ መጠቀም ከሚቻልባቸው ግብይቶች ላይ ተቀናሽ የሚደረገው 2 % ቅድመ ግብር ብቻ ነው።
- ግብር ለተቀነሰበት ሰው ተከታታይ ቁጥር ያለው ደረሰኝ መስጠት።
- ተቀናሽ የሚደረገው 2% እና 30% ግብር የሚሰላበት የዕቃው ወይም የአገልግሎቱ ጠቅላላ የክፍያ መጠን የግብይቱ ላይ የሚከፈሉ የመንግስት ታከሶችን (እንደተጨማሪ እሴት ታክስ እና ተርን ኦቨር ታክስ የመሳሰሉትን) እና በሻጭ ገቢ ውስጥ የማይካተቱ ክፍያዎችን ሳይጨምር ነው።

3. ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሰው እንዲያስቀሩ ሃላፊነት የተሰጣቸው ሰዎች

- በገቢ ግብር አዋጁ ቁጥር 979/2008 አንቀፅ 92 (1) ፣ በመመሪያ ቁጥር 2/2011 አንቀጽ 8 እና በመመሪያ ቁጥር 145/2011 አንቀጽ 3 በተገለፀው መሰረት በግዥ ወቅት ከሚፈጽሙት ክፍያ ላይ ግብር ቀንሰው እንዲያስቀሩ ግዴታ የተጣለባቸው ሰዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው፦
  1. በህግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች፡- የአክሲዮን ማህበር፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፣ የሽርክና ማህበር፣ የህብረት ስራ ማህበር……ወዘተ፣
  2. የመንግስት መ/ቤቶች፡- በፌደራል እና በክልል የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ መሰረት ለመንግስት መ/ቤቶች በተሰጠው ትርጉም ውስጥ የሚካተቱ ወይም በተቋቋመበት ህግ የመንግስት መ/ቤት የተባሉ የፌደራል፣ የክልል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የድሬዳዋ አስተዳደር የመንግስት መ/ቤቶች፣
  3. ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች፡- ለትርፍ ላልሆነ ለተለያዩ ዓላዎች የተቋቋሙ ማህበራትና የሃይማት ድርጅቶች።

4. መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፡- በሲቪክ ማህበራት አዋጅ መሰረት የተቋቋሙ ‹‹የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች›› ወይም ‹‹የኢትዮጵያ ማህበሮች›› ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ በውጭ አገር የተቋቋሙ ተመሳሳይ ድርጅቶች፣

5. የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት በምርት ገበያው አማካኝት ከሚከናወን ግብይት ጋር በተያያዘ ገዥውን በመወከል የሚፈፅመው ግብይት

6. ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የንግድ ትርፍ ግብር ቀንሰው ገቢ እንዲያደርጉ ሃላፊነት የተሰጣቸው የደረጃ “ሀ” ግለሰብ ግብር ከፋዮች ባለፉት ሶስት ተካታታይ ዓመታት በአማካይ 10 ሚሊዮንና ከዚያ በላይ ጠቅላላ ገቢ ያስመዘገቡ ግለሰብ ግብር ከፋዮች ናቸው ።

7. ቀጥሎ በተመለከቱት የንግድ ስራ ዘርፎች የተሰማሩ የደረጃ “ሀ” ግብር ከፋዮች ዓመታዊ ሽያጫቸው ከግምት ውስጥ ሳይገባ ግብር ቀንሰው የማስቀረት ግዴታ አለባቸው፡-

(ሀ.) ማንኛውም ባለ ኮከብ ሆቴል ወይም ማንኛውም ሪዞርት፣

(ለ) ከ1 እስከ 4 ደረጃ ያላቸው ስራ ተቋራጮች፣

(ሐ). ማንኛውም ሪል ስቴት አልሚ ፣

(መ). የምግብ አምራች ኢንዱስትሪዎች ፣

(ሠ). በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ግዢ የሚፈፅም ማንኛውም ግለሰብ ግብር ከፋይ በምርት ገበያው በኩል ላደረገው ግብይት ብቻ፣

(ረ). ሆስፒታሎች እና በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መስፈርት መሰረት ከፍተኛ እና ከዚህ በላይ ያላቸው ክሊኒኮች

(ሰ). ዩኒቨርሲቲዎች እና ኮሌጅ እና

(ሸ). ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ምርት በመረከብ የሚያከፋፍል ማንኛውም ግለሰብ ግብር ከፋይ።

4. ግብር ቀንሶ የመያዝ ግዴታ የማይመለከታቸው ሰዎች ፡-

የሚከተሉት በግዢ ወቅት ከሚፈጽሙት ክፍያ ላይ ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ የለባቸውም።

- ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች፤
- ላኪዎች/ ወደ ውጭ ለሚልኳቸው ምርቶች በግብዓትነት ለሚያገለግሉ እቃዎች ብቻ/
- በዲፕሎማቲክ እና አለም አቀፍ ስምምነት መሰረት የተቋቋሙ ድርጅቶች፣ የውጭ ዲፕሎማቲክ ኮንሱላር ሚሲዮኖች፣ ኤምባሲዎች፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አካላት እና የዲፕሎማቲክ መብት ያላቸው ተመሳሳይ አካላት፣
- የገቢዎች ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ቅድመ ግብር የመያዝ ግዴታ ከተጣለባቸው ግለሰብ ግብር ከፋዮች ውጪ ያሉ ግለሰብ ግብር ከፋዮች (መመሪያ ቁጥር 145/2011 አንቀጽ 3 የተገለጸው)

5. ግብር ቀንሶ የመያዝ ሥርዓት ተፈፃሚ የማይደረግባቸው ግብይቶች

ሀ. የሰው ወይም የእንስሳት ህክምና አገልግሎት

ለ. የመደበኛ ትምህርት አገልግሎት (ሥልጠናን አይጨምርም)

ሐ. የፋይናንስ አገልግሎት/ ባንክ የደንበኞቹ ንብረት ሲሸጥ የሚቀበለውን ክፍያ አይጨምርም)

መ. የኤሌክትሪክ አገልግሎት

ሠ. የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት

ረ. የየብስ፣ የአየር፣ የባህር እና የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት/ ኪራይ አይጨምርም

ሰ. የውሃ አገልግሎት/ ታሽጎ የሚሸጥ ውሃን አይጨምርም/

ሸ. ከገቢ ግብር ነፃ መብት (Tax holiday) የተሰጣቸው ኢንቨስተሮች ከግብር ነፃ በሆኑበት ጊዜ ውስጥ የሚሠጡት አገልግሎት ወይም የሚያቀርቡት ዕቃ

ቀ. ከገቢ ግብር አዋጅ መሰረት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ተቀናሽ የሚደረግባቸው የሰንጠረዥ “መ” ገቢዎች፣

በ. የነዳጅ አቅርቦት /ቅባት እና ዘይቶችን አይጨምርም/

ተ. በፌድራል እና በክልል የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ መሰረት ለመንግስት መ/ቤት በተሰጠው ትርጉም ውስጥ የሚካተቱ ወይም በተቋቋመበት ህግ የመንግስት መ/ቤት የተባሉ የፌደራል የክልል፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የድሬዳዋ አስተዳደር መንግስት መ/ቤቶች

ቸ. ለትርፍ ያልተቋቋሙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ማህበራት የሚያቀርቧቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች(ከተቋቋሙበት አላማ ውጪ በንግድ መልክ የሚያቀርቧቸውን ዕቃዎችና አገልግሎቶች አይጨምርም)

ኃ. ከገቢ ግብር ህግ መሰረት ከግብር ነጻ ከሆነ ገቢ

ነ. ከመንግስት በተሰጣቸው ውክልና መሰረት ዕቃ ወይም አገልግሎት የሚያቀርቡ ድርጅቶች፣ወ.ዘ.ተ መ.ቁ 2/2011

6.ግብሩን ቀንሶ እንዲያስቀር ግዴታ የተጣለበት ሰው ተግባርና ኃላፊነት

- በአገር ውስጥ ከሚፈጸሙ ክፍያዎች ላይ በወሩ ውስጥ ተቀናሽ ያደረገውን አጠቃላይ ግብር ከቀጣዩ ወር የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ባለስልጣኑ ባዘጋጀው ቅጽ መሰረት ገቢ ማድረግ ይጠበቅበታል፣

ለምሳሌ.

- X ኃላ.የተ.የግል.ማህበር ለሰራተኞቻቸው የ400,000 ብር የደንብ ልብስ ግዥ ቢፈፅሙ ሻጩ/አቅራቢው የእጅ በእጅ የሽያጭ ደረሰኝ ወይም የካሽ-ሬጂስተር ደረሰኝ ከሰጣቸው ከሚከፍሉት ክፍያ ላይ 2% ቀንሰው በማስቀረት ለባለስልጣኑ ዊዝሆልድንግ ታክስ መክፈል አለባቸው ማለት ነው፡፡
- በዚህ ምሳሌ የ400,000.00 ብር 2%= 8000.00 ብር ይሆናል፤ስለዚህ ገዥዎቹ ወገኖች ለሻጩ ከሚከፍሉት ክፍያ ላይ 8000 ብር ማስቀረት 8ሺውን ለመንግስት ግብር እንዲሁም (400,000.00 ብር - 8000.00) ብር392,000.00 ለሻጩ መክፈል አለባቸው ማለት ነው፡፡
- ሆኖም ግን ሻጭው የታክስ መለያ ቁጥሩን እና የፀና ንግድ ፈቃድ ካልሰጠ የግዥውን ጠቅላላ ክፍያ 400,000*30% = ብር120,000 ለመንግስት ግብር እንዲሁም 400,000-120,000 = 280,000 ብር ለሻጭው መክፈል ይኖርበታል ማለት ነው፡፡

7. ከተከፋይ ሂሳብ ላይ  ግብር ቀንሶ አለመያዙ፣ አለማሳወቁ ወይም አለመክፈሉ ያለው ህጋዊ ውጤት:-

- ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ታክስ ቀንሶ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ማስተላለፍ ያለበት ማንኛውም ሰው ሳይቀንስ የቀረውን ወይም ቀንሶ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ያላስተላለፈውን 10% (አስር በመቶ) ቅጣት ይከፍላል ፡፡
- የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ፣ ዋና የሂሳብ ሹም ወይም ታክስ ቀንሶ መያዝ እንዳለበትና የተያዘውን ታክስ መክፈል ያለበት ማንኛውም ሰው እያንዳንዳቸው **2** ሺህ ብር ቅጣት ይከፍላሉ፡፡

- በገቢ ግብር አዋጁ አንቀፅ **97(4)** መሰረት የከፈለውን ፍሬ ግብር ክፍያ ከተፈፀመለት ሰው ላይ የማስመለስ መብት አለው፡፡ የማስመለስ መብት ያለው የከፈለውን ፍሬ ግብር ብቻ ነው፡፡ የከፈለውን ወለድና ቅጣት ማስመለስ አይችልም፡፡
- በደንብ ቁጥር **410/2009** አንቀፅ **64(1)** እና **(2)** መሰረት የዊዝሆልድንግ ታክስ ለባለስልጣኑ የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው ታክሱን ያልከፈለ ቢሆንም ዋናው ግብር ከፋይ ግብሩን የከፈለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ካቀረበ ግን መክፈል የነበረበትን ፍሬ ግብር ክፈል አይባልም፡፡ ምክንያቱም ከመጀመሪያው በዊዝሆልድንግ ታክስ ፅንሰ ሀሳብ ውስጥ ዋናው ግብር ከፋይ ሻጩ/አቅራቢው ወገን ስለሆነ ነው፡፡

# ተርን ኦቨር ታክስ

## 1. የታክሱ አስፈላጊነት

- በንግድ ግንኙነት ውስጥ ፍትኃዊነትን ለማስፈን ፣
- ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገቡ ሰዎች ግዴታቸውን እንዲወጡ ለማስቻል ፣
- የታክስ ስርዓቱን ሽፋን የተሟላ ለማድረግ።

# 2. የታክሱ ተፈጻሚነት

- ከታክሱ ነጻ ከተደረጉት በስተቀር ፣ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገቡ ሰዎች በአገር ውስጥ በሚሸጧቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች
- ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ የተደረጉት ግብይቶች ከተርን ኦቨር ታክስም ነጻ ተደርገዋል።

# 3. ከታክሱ ነፃ የሆኑ አቅርቦቶች ( Exempt supplies )

- ከታክሱ አዋጅ አንቀጽ 7 እና በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ከታክሱ ነፃ የተደረጉት አቅርቦቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

o ቢያንስ ሁለት ዓመት ያገለገለ መኖሪያ ቤት ሽያጭ እና የመኖሪያ ቤት ኪራይ፤

o የፋይናንስ አገልግሎቶች፣

# ከታክሱ ነፃ የሆኑ አቅርቦቶች (Exempt supplies). . ..የቀጠለ

- በሃይማኖት ድርጅቶች የሚሰጡ የእምነት ወይም ከአምልኮት ጋር የሚገናኙ አገልግሎቶች፣
- የሕክምና አገልግሎት እና በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በሚወጣ መመሪያ መሠረት
  - በሐኪም የሚታዘዙ መድሃኒቶች፣
- የህክምና አቅርቦቶች እና የህክምና መገልገያዎች፣
- በትምህርት ተቋማት የሚሰጡ የማስተማር አገልግሎቶች
- ለሕፃናት ጥበቃ በመዋለ ሕፃናት የሚሰጡ አገልግሎቶች፣

# ከታክሱ ነፃ የሆኑ አቅርቦቶች . . . የቀጠለ

- በሰብዓዊ እርዳታ መልክ የሚቀርቡ ዕቃዎች እና የሚሰጡ አገልግሎቶች

- የኤሌክትሪክ፣ የኬሮሲንና የውሃ አገልግሎቶች፣

# ከታክሱ ነፃ የሆኑ አቅርቦቶች . . . የቀጠለ

- የትራንስፖርት አገልግሎት፣
- ማናቸውም የሥራ እንቅስቃሴ ለማከናወን ለሚሰጥ ፈቃድ

  ለመንግስት የሚፈፀም ክፍያ፣

# ከታክሱ ነፃ የሆኑ አቅርቦቶች . . . የቀጠለ

- ከስድሣ በመቶ ሠራተኞቹ አካል ጉዳተኞች የሆኑበት አካል ጉዳተኞችን ቀጥሮ የሚያሠራ ድርጅት የሚያቀርባቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች፣
- ወደ አገር የሚገቡና በአገር ውስጥ የሚሸጡ መፃህፍትና የታተሙ ጽሁፎች

# ከታክሱ ነፃ የሆኑ አቅርቦቶች . . . የቀጠለ

- ከታክስ ነፃ የሆኑ ግብይቶች ማለት አቅርቦቶችን ከተርን ኦቨር ታክስ ክፍያ ነፃ ማድረግ ነው፡፡
  - ✓ በመሆኑም ከታክስ ነፃ በተደረጉ ግብይቶች ላይ ተርን ኦቨር ታክስ አይከፈልም፡፡

## 4. የታክስ ምጣኔ

- በማናቸውም በአገር ውስጥ በሚሸጡ ዕቃዎች ላይ 2% (ሁለት በመቶ)፣
- በአገር ውስጥ በሚሰጡ አገልግሎቶች ላይ ፣
  - ✓ ሥራ ተቋራጮች የእህል ወፍጮ ቤቶች፣ የትራክተሮች እና ኮምባይን ሀርቨስተሮች አገልግሎት 2 % (ሁለት በመቶ) ፣
  - ✓ ሌሎች 10 % (አስር በመቶ)

## 5. የታክሱ ስሌት መሠረት

ታክሱ የሚሰላበት ዋጋ የዕቃው ወይም የአገልግሎቱ ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ ነው።

## 6. የታክስ ማስታወቂያ ማቅረቢያና መክፈያ ጊዜ

- እያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የታክስ ማስታወቂያ መቅረብ አለበት
- ታክሱም ለታክስ ማስታወቂያ ማቅረቢያ በተሰጠ የጊዜ ገደብ ውስጥ መከፈል አለበት
- የሂሳብ ጊዜ ፡-
  - ✓ የደረጃ ሀ ግብር ከፋዮች በየወሩ ፣
  - ✓ የደረጃ ለ ግብር ከፋዮች  በኢትዮጵያ በጀት ዓመት ፣ ወይም በአውሮፓ ዘመን አቆጣጠር ከዓመቱ የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ የሚቀጠር የሦስት ወር ጊዜ ፣
  - ✓ የደረጃ ሐ ግብር ከፋዮች የበጀት አመቱ ።

## 7. የሂሳብ መዝገብ

በገቢ ግብር አዋጅ የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ የተጣለባቸው ታክስ ከፋዮች ለተርን ኦቨር ታክስ አወሳሰን እንዲያገለግል በአዋጁ የታዘዘውን የሂሳብ መዝገብ መያዝ አለባቸው፡፡

# የተጨማሪ  እሴት ታክስ አዋጅ ቁ.1157/2011

## የተዘጋጀ ግንዛቤ ማስጨበጫ

# የሰነዱ ይዘት

- የተጨማሪ እሴት ታክስ ምንድነው ?
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ጠቀሜታዎች ?
- ታክሱ የሚጣልባቸው አቅርቦቶች ?
- የታክሱ ከፋዮች ?
- ከታክሱ ነፃ የሆኑ አቅርቦቶች ?
- ታክስ ስለመጣል ?

# 1.የተጨማሪ እሴት ታክስ ምንድነው?

- የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) በፍጆታ ላይ ወይም በተጠቃሚው ወጪ ላይ የተመሠረተ ታክስ ነው።
- የሚሰበሰበው ወይም የሚቀረጠው ምርት ከውጭ አገር ወደ አገር ውስጥ ሲገባ ወይም የዕቃና የአገልግሎት ግብይት ሲካሄድ ነው።
- ታክሱ ከአስመጪዎችና ጥሬ ዕቃ አምራቾች አንስቶ እስከ ችርቻሮዎች ድረስ በሚደረጉ የማምረትና የማከፋፈል /የማሠራጨት/ ሂደቶች በሁሉም ደረጃዎች፣ በሚፈጠረው ተጨማሪ እሴት ላይ ይሰበሰባል።

# የተጨማሪ እሴት ታክስ ምንድነው.....የቀለጠ

በዚህም ምክንያት፡-

- ምርት ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላው በሚተላለፍበት ወቅት የታክስ ተንከባላይነት ባህሪይ ቀደም ብሎ የተከፈለውን ታክስ በማቀናነስ በታክስ ላይ ታክስ የማሰብ ሁኔታ እንዳይፈጠር ያደረጋል፣
- ቀድሞ የነበረው የሽያጭ ታክስ በጥሬ ዕቃ ላይ የተከፈለን ታክስ ብቻ ተመላሽ የሚያደርግ ሲሆን፣
- በተጨማሪ እሴት ታክስ ግን ለማምረቻ መሣሪያዎች፣ ለማከፋፈልና ለአስተዳደራዊ ተግባራት የተከፈለ ታክስን ጭምር ተመላሽ ያደርጋል፡፡

# 2.የተጨማሪ እሴት ታክስ ጥቅሞች

- በአገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶች ከውጭ ከሚገቡ ምርቶች ጋር ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ይረዳል፣
- ለካፒታል ዕቃዎች የሚደረገው የታክስ ተመላሽ ኢንቨስትመንትን ያበረታታል።
- ወደ ውጭ በሚላኩ ምርቶች ላይ
  - ✓ተፈፃሚ የሚሆነው መጣኔ (Rate) ዜሮ በመቶ /0%/ ስለሆነ እና
  - ✓ለግብዓቶች የተከፈለው ታክስም ተመላሽ የሚደረግ በመሆኑ

# የተጨማሪ እሴት ታክስ ጥቅሞች .....የቀለጠ

- የአገሪቱ ምርቶች በአለም አቀፍ ገበያዎች ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆኑና የውጭ ንግድ እንዲበረታታ ያደርጋል።
- የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈፃፀም በደረሰኝ ላይ ተመስርቶ የሚከናወን በመሆኑ
  - ✓ በቀላሉ ሳይከፈል ሊታለፍ ወይም
  - ✓ ሊጭበረበር የሚችል ታክስ ባለመሆኑ የታክስ ፍትሐዊነት በተሻለ አኳኋን ያስጠብቃል።

# 3.ታክሱ የሚጣልባቸው አቅርቦቶች (Taxable supplies)

- በአዋጁ አንቀጽ 7 መሠረት ታክሱ የሚጣለው በተመዘገበ ሰው የሚከናወን ማናቸውም ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ነው፡፡
- ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ማለት ደግሞ
  - ✓ በህጉ ነፃ ከተደረጉት በስተቀር፤
  - ✓ ታክስ የሚከፈልበትን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት
  - ✓ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚቀርብ ዕቃ ወይም አገልግሎት ነው፡፡
- ስለሆነም ስለ ዕቃዎች አቅርቦት እና አገልግሎት መስጠት ትርጉም የሚሰጠው የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ አንቀጽ ለታክሱ አፈፃፀም ቁልፍ ነው፡፡

# ታክሱ የሚጣልባቸው አቅርቦቶች . . . የቀጠለ

- በታክስ አዋጁ አንቀጽ 6 መሠረት " ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ" ማለት ፤-
  - ለትርፍ የተከናወነ ቢሆንም ባይሆንም ጥቅም ለማግኘት ሲባል ለሌላ ሰው በሙሉ ወይም በከፊል ዕቃ የመሸጥ ወይም አገልግሎት የመስጠት ተግባርን ለማከናወን በማሰብ ወይም በትክክል በማከናወን ማንኛውም የተመዘገበ ሰው በመደበኛም ሆነ መደበኛ ባልሆነ መንገድ የሚያከናውነው የስራ እንቅስቃሴ ነው።

# ታክሱ የሚጣልባቸው አቅርቦቶች. . . የቀጠለ

- ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ተደርገው የሚቆጠሩ
  - የተመዘገበ ሰው ታክስ ለሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የገዛቸውን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ለሌላ አገልግሎት እንዲውሉ ያደረገ እንደሆነ፤
  - አሠሪው ለሠራተኞቹ በስጦታ ወይም በሌላ ማናቸውም አኳኋን የሚያቀርባቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች፣
  - ምዝገባ ሲሰረዝ የካፒታል ዕቃዎችን ጨምሮ ሥረዛው በተከናወነበት ጊዜ በተመዘገበው ሰው እጅ የሚገኙ ዕቃዎች፣
  - ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ አንድ ክፍል ሆኖ ተለይቶ በራሱ የሚንቀሳቀስ ክፍል የተሸጠ እንደሆነ፣

# ታክስ የማይከፈልበት የንግድ ስራ እንቅስቃሴ

- ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ስራ እንቅስቃሴ ተደርገው የማይወሰዱ፡-
  - ለታክሱ የተመዘገበ ሰው ዕቃዎቹን ለማግኘት የከፈለው ታክስ ተቀናሽ እንዲደረግ ያልተፈቀደ ሲሆንና በኃላ የሚደረግ የእነዚህ ዕቃዎች ሽያጭ፣

# የተጨማሪ እሴት ታክስ መጣኔዎች /Rates

- ሁለት የታክስ መጣኔዎች ይኖሩታል። እነሱም 15 ከመቶ መደበኛ መጣኔና ዜሮ ከመቶ መጣኔ (በታክስ መረብ ውስጥ የታቀፉ መሆናቸውን ለመግለጽ) የሚባሉት ናቸው።






# …መጣኔዎች…

- **15** በመቶ መጣኔ
  - በተመዘገቡ ሰዎች የሚከናወን ታክስ የሚከፈልበት ግብይት፡-
    - “ታክስ የሚከፈልበት ግብይት” ማለት ከታክስ ነፃ ከተደረገው አቅርቦት በስተቀር ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት የሚከናወን ማናቸውም የዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች አቅርቦት ነው፡፡

# ...መጣኔዎች...

- ✓ በተመዘገበ ሰው ስለሚከናወን ታክስ የሚከፈልበት ግብይት የተቀመጠው መመዘኛ ባልተመዘገቡ ሰዎች የሚከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት የተጨማሪ እሴት ታክስ እንደማይመለከተው ያመለክታል፡
- ✓ ሆኖም የተመዘገበ ሰው የንግድ ስራ ዕቃዎቹን ለግል ጥቅም ያዋላቸው ከሆነ የነዚህ ዕቃዎች አቅርቦት ታክስ ለሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ እንዳዋላቸው ይቆጠራል።

# 4.የታክሱ ከፋዮች

➢ በታክሱ ህጉ አፈፃፀም ታክስ ከፋዮች የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፤

o የተመዘገበ ሰው የሚባሉት:- የተመዘገበ ወይም መመዝገብ ያለበት ሰው፣

o ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባ ፣

o ወደ አገር የሚገቡ አገልግሎቶችን በሚመለከት በታክሱ አዋጅ በአንቀጽ 23(በገዥው ስለሚሰበሰብ ታክስ)መሠረት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ የሆነ ሰው፣

➢ በታክሱ የተመዘገበ ሰው ምዝገባው ከሚፀናበት ቀን ጀምሮ ታክስ ከፋይ ነው።

➢ መመዝገብ ያለበት ሆኖ ያልተመዘገበ ሰው ደግሞ የምዝገባ ግዴታ ከሚጀምርበት ጊዜ ቀጥሎ ያለው የሂሳብ ጊዜ ከሚጀምርበት አንስቶ ታክስ ከፋይ ነው።

# 5. ከታክሱ ነፃ የሆኑ አቅርቦቶች ( Exempt supplies )

- በታክሱ አዋጅ አንቀጽ 8 እና በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ከታክሱ ነፃ የተደረጉት አቅርቦቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡
  - ቢያንስ ሁለት ዓመት ያገለገለ መኖሪያ ቤት ሽያጭ እና የመኖሪያ ቤት ኪራይ፤
  - የፋይናንስ አገልግሎቶች፣
    - ኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚቀርብ ወርቅ ወደ አገር ማስገባት፣
    - ሃይማኖት ድርጅቶች የሚሰጡ የእምነት ወይም ከአምልኮት ጋር የሚገናኙ አገልግሎቶች፣

# ከታክሱ ነፃ የሆኑ አቅርቦቶች (Exempt supplies). . ..የቀጠለ

- የሕክምና አገልግሎት እና በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በሚወጣ መመሪያ መሠረት በሐኪም የሚታዘዙ መድሃኒቶች፣
- የህክምና አቅርቦቶች እና የህክምና መገልገያዎች፣
- በትምህርት ተቋማት የሚሰጡ የማስተማር አገልግሎቶች (ስልጠናዎችን አያካትትም)
- ለሕፃናት ጥበቃ እንዲሁም በመዋለ ሕፃናት የሚሰጡ አገልግሎቶች፣

# ከታክሱ ነፃ የሆኑ አቅርቦቶች . . . የቀጠለ

- የኢንዱስትሪ አደጋዎችና በድንገት ለደረሱ ጉዳቶች መልሶ ማቋቋሚያ ተግባር እንዲውሉ ለመንግስት አካላት እና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች የሚሰጡ ከውጪ አገር የሚገቡ ዕቃዎች፣
- የኤሌክትሪክ፣ የኬሮሲንና የውሃ አገልግሎቶች፣
- ከልዩ ልዩ የአገልግሎት ወይም የኮሚሽን ክፍያዎች በስተቀር የፖስታ አገልግሎት ድርጅት በማቋቋሚያ አዋጁ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የሚያቀርባቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች፤

# ከታክሱ ነፃ የሆኑ አቅርቦቶች . . . የቀጠለ

- የትራንስፖርት አገልግሎት፣
- ማናቸውም የሥራ እንቅስቃሴ ለማከናወን ለሚሰጥ ፈቃድ ለመንግስት የሚፈፀም ክፍያ፣
- ከስልሣ በመቶ በላይ ሠራተኞቹ አካል ጉዳተኞች የሆኑበት አካል ጉዳተኞችን ቀጥሮ የሚያሠራ ድርጅት የሚያቀርባቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች፣

# ከታክሱ ነፃ የሆኑ አቅርቦቶች . . . የቀጠለ

- ወደ አገር የሚገቡና በአገር ውስጥ የሚሸጡ መፃህፍትና የታተሙ ጽሁፎች
- የጡረታ አበል ክፍያ አገለግሎት፣
- የጉዞ ወኪሎች የአውሮፕላን ቲኬት በመሸጥ የሚሰጡት የገበያ አገልግሎት፣

- በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩትን ዘርፎች ምርቱን ለማምረት ወይም አገልግሎቱን ለመስጠት በተከናወኑ ግዥዎች /ግብአቶች/ ላይ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማካካሻ /ተመላሽ/ ሊጠየቅበት እንዲሁም ቫት ሊሰበሰብበት አይችልም።

# 6. ታክስ ስለመጣል

- ✓ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ታክሱ እንዲጣልበት የሚደረገው በተመዘገበ ሰው የሚከናወን ሲሆን ብቻ ነው፡፡
- ✓ ታክስ በሚከፈለበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የተሰማራና ለምዝገባ ከተወሰነው የገንዘብ ጣሪያ በላይ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት የሚያከናውን ወይም እንደሚያከናወን የሚጠበቅ ማናቸውም ሰው በህጉ መሠረት የመመዝገብ ግዴታ አለበት፡፡

# ታክስ ስለመጣል . . . የቀጠለ

6.2.ከዚህ በታች የተመለከቱ ግብይች በዜሮ መጣኔ /0%/ ታክስ ይከፈለባቸዋል።

ሀ.ለውጭ የገበያ የሚቀርቡ ዕቃዎችና አገልግሎቶች (Exports)

ለ.ዓለም አቀፍ የዕቃ ወይም የሰዎች የማጓጓዝ ተግባር፣ እንዲሁም በጉዞው አገልግሎት ላይ የሚውሉ የፍጆታ አቅርቦቶች

ሐ.ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚቀርብ ወርቅ፣

መ. አንድ የተመዘገበ ሰው ለሌላ የተመዘገበ ሰው አንድ ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ወይም ራሱን ችሎ የሚሰራ ታክስ የሚከፈልበት የንግድ እንቅስቃሴ አብዛኛውን ክፍል /ሀብት/ ላልተወሰነ ጊዜ ይንቀሳቀሳል ተብሎ ለተቋቋመ ድርጅት ሲያስተላለፍ

# ታክስ ስለመጣል . . . የቀጠለ

- ዜሮ ከመቶ መጣኔ /0%/ ታክስ ይከፈልባቸዋል ሲባል በመሠረቱ ከእነዚህ ግብይቶች የተጨማሪ እሴት ታክስ አይሰበሰብም ማለት ነው።
- ይሁንና አቅርቦቶቹ የሚቆጠሩት ታክስ እንደሚከፈልባቸው አቅርቦቶች (Taxable Suppiles) ሲሆን፣ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት ለመመዝገብ በአጠቃላይ ዓመታዊ ሽያጭ ውስጥ ይታሰባሉ።
- እንደዚሁም እነዚህን አቅርቦቶች የሚያመርትና አገልግሎት የሚሰጥ ሰው በግብዓት ላይ የከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ማካካሻ/ተመላሽ ለማግኘት ይችላል።

ማጠቃለያ:-

- ንግድ ፍቃድ ካወጡ ከቀጣይ **ወር** ጀምሮ **የተርን ኦቨር ታክስ** /TOT/ በየወሩ ማሳወቅ
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ከሆኑ በማናቸውም የ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ያከናወነው **ጠቅላላ ሽያጭ ብር 70,000,000(ሰባ ሚሊዮን)** እና ከዚህ በላይ ለሆነ ታክስ ከፋይ **በወሩ**፣
- በማናቸውም **የ12 ወራት** ጊዜ ውስጥ ያከናወነው ጠቅላላ ሽያጭ **ከብር 70,000,000(ሰባ ሚሊዮን)** በታች የሆነ ታክስ ከፋይ **በየ3 ወር ሪፖርት** ማድረግ ይጠበቅበዎታል።
- የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ወዲያውኑ መግዛት እንዳለብዎት አይርሱ
- ደረሰኝ ከማሳተምዎ በፊት ለማተሚያ ቤት የህትመት ፍቃድ መውሰድ
- ማንኛውም ኃ/የተ/የግ/ማህበር ሆኖ ለግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የተመዘገበ ድርጅት ከ3000 ብር በላይ አገልግሎት ከ 10,000.00 ብር በላይ የዕቃ ግዥ የፈፀመ እንደሆነ በፈፀመው ግዥ መጠን ቅድመ ታክስ ግብር እንደሆነ በፈፀመው ግዥ መጠን ቅድመ ታክስ ግብር በመቀነስ ማሳወቅ የሚጠበቅባችሁ መሆኑን ስንገልፅ ግዥው **ንግድ ፍቃድ እና ቲን ሰርተፍኬት ካላቸው ሰዎች የተገዛ ግዥ ከሆነ 2% ንግድ ፍቃድ እና ቲን ሰርተፍኬት ከሌላቸው ሰዎች የተገዛ ግዥ 30% በመቀነስ ግዥ** ከተፈፀመበት ወር ቀጥሎ ባለው ወር ገቢውን ማሳወቅ የሚጠበቅባችሁ መሆኑን።

# THANK YOU